## የዘመኑ ካህን፣(ለሃይማኖት ተቆርቋሪ ከሆኑት አንዱ ነኝ) ፩

የዘመኑ ካህን ጥምጣም ያወለከው፣

የእግዜርን ስም ጠርተህ በመስቀል ሳትባርከው፣

የሰጡህን ሁላ ዝም ብለህ በላሃው፣

አንተ ራስህ ረክሰህ ህዝቡን አስረከስከው፣

የአቡነ ጴጥሮስ የአቡነ ሚካኤል፣

ይውቀስህ አጽማቸው።

    መስቀሉን ጨብጠህ

    ዳዊትህን አንግበህ፣

    ልክ እንደ አባቶችህ፣

    በአንድ ላይ ሰብስበህ፣

    ሕዝቡንም ባርከህ

    ታግለህ አታግል በግንባር ቁመህ።

አንተ ቅደምና ቀድሰህ ተቀደስ፣

ዝምብለህ አትይ ሃይማኖትህ ስትረከስ፣

ጥምጣምህን አውልቀህ ቃልኪዳን አታፍርስ፣

አቡነ ሚካኤል፣ አቡነ ጴጥሮስ፣

በአካል ባይሆንም ያዩሃል በመንፈስ።

    መስቀሉን ጨብጠህ በእምነትህ ጽና፣

    ፍርድ የሚሰጥበት ጊዜው ቀርቦአልና፣

    በግንባር አስከብር የሰውን ስብዕና፣

    ለሃይማኖት ስትል ለሀገር ህልውና።

አንተን እንዳይወቅሱህ ከሙታን ተነስተው፣

ለእትምነት ለሀገር ህይወታቸው ያለፈው፣

የአቡነ ጴጥሮስ ሲነገር ገድላቸው፣

የአቡነ ሚካኤል ሲዘከር ስማቸው፣

አንተ ግን ታፍራለህ እምነት ያስረከስከው።

EthioLion.Com

እነሱ ሲሰው ለሀገር ለሃይማኖት፣
በአህዛብ መዳፍ እሪያ በነካበት፣
አናስነካም ብለው ቤት ክርስቲያንን፣
እነሱ ተባርከው አስባረኩት ሕዝቡን።

ሥጋቸውን ጎድተው ነፍሳቸውን አዳኗት፣
እስካሁን የቆየን ጸንተን በሃይማኖት፣
ቢጠብቀነ አይደል የእነሱ እምነት ጸሎት፣
የጸዳውን ትተን በኢትዮጵያ መሬት፣
በልተን አልነበረም አሳማና ድመት።

<u>ወደፊት ሳይሆንስ ወደ ኋላ እያየ፣</u>

በዓለም የሚሰራው ህሊናውን ማርኮት፣
ቅኔ ያስቀኘውን ገዳምና አድባራት፣
አልፈልግም ብሎ የነፍሱን መድሃኒት፣
ከተማ ውስጥ ገባ ማተቡን አውልቋት፣
ቀሚሱን አጥልቆ ከቤት ወደ አንዱ ቤት፣
ሲፏንን ይውላል ሥጋውን ለማርካት።

አሁንስ አሰጋኝ ግብረ ቀሳውስት፣
አሁንስ አስፈራኝ ግብረ ዲያቆናት፣
ጭራሹን ደነገጥኩ በአሉት ጳጳሳት፣
ከመስመሩ ወጥቶ ሲሸሽ ሲሸራተት፣
እየተወ ሲሄድ የአባቶቹን እምነት።

ተባባሪ ሁነው ለአለው መጥፎ ስርአት፣
ከአህዛቦች ጋር አብረው በመዶለት፣
በተቀደሰችው እርኩሱ ሲቆምባት፣
ሰዶምን ገሞራን በግብር ሲያስመስላት፣
ዝምታን መርጠዋል የዘመኑ ካህናት
ከሰማዩ ወርዶ እንዳይበላን እሳት፣
ቆብ በጫኑት ሰበብ በመነኮሱት፣
ጥቅም በገዛቸው ብዙ ሊቃውንት።

EthioLion.Com

ተርበው ተጠምተው እውቀትን ለማግኘት፣

ድጓ ጾመ ድጓ፣ ቅኔን ሰዓታት፣

እነሱ ተምረው ህዝቡን ሊያስተምሩት፣

ቃል ኪዳን አድርገው ከላይኛው አባት፣

ቆይተው ነበረ ለረጅም ዘመናት።

<u>አሁንስ የሚገርም፣</u>

ሁሉን ነገር ትተው ጣል እርግፍ አድርገው፣

ከእሷ ያገኙትን ኪዳን አፍርሰው፣

ከነፍሳቸው ይልቅ ለሥጋቸው ሳስተው፣

እየወጡ ሄዱ ቤተ ክርስቲያን ዘግተው

ለሐሳዊ ካህን ቁልፉን አስረክበው።

ቅድስት ተዋህዶ ስርአቷ ሲረክስ፣

የወታደር ዲያቆን የደህንነት ቄስ፣

መነኩሴ ነኝ ብሎ ታየ መቅደስ፣

በውስጥ ቀሚሱ ሽጉጡን አጥልቆ፣

ገባ ወደ መቅደስ በደም ተጨማልቆ፣

ሐቀኛውን ካህን ከግቢው አርቆ።

<u>የቀሩትም ደግሞ፣</u>

አለቃ ኢያሌውን መምሰል አቅቶአቸው፣

አለማዊ መሆን የዘመኑ አምሮአቸው፣

ጾጥ ብለው ተገዙ ለተኩላው መሪያቸው።

ሱፍ ቦላሌ ለብሰው እስከ እግር ጣት፣

ገበርዲና ለብሰው ኮትና ከረባት፣

ዝንጥ ብለው ወጡ ያንን ለማሳየት፣

ያላዩትን ሊያዩ ገቡ መሸታ ቤት፣

ያልተፈቀደውን ለነእሱ ሊቀምሱት፣

ጮማ እያስቆረጡ ውስኪ መጠጣት፣

ቤተ ክርስቲያን ቀርቶ ዳንስ ቤት ማምሸት፣

ከቃለ እግዚአብሔር ውጭ በመማር ክሕደት፣

EthioLion.Com

<u>ከሆነ ሥራና አላማቸው፣</u> ፬

እነሂህን  ካህናት ምን እንበላቸው?

ሕዝብን ማደናገር ከእንግዲህ ይብቃችሁ፣

ብላችሁ ተነሱ ምእመናን ሁላችሁ፣

በአንድ ላይ እንቁም አንድ ይሁን ድምጻችሁ።

እውነተኛ ካህን ቢሆኑማ ኑሮ፣

ቤተ ክርስቲያን ሲቃጠል፣

ንዋየ ቅድሳት ሲወሰድ ተዘርፎ፣

አያዩም ነበረ አንገት አቀርቅሮ፣

ያሰሙ ነበረ ለእግዚአብሐር እሮሮ።

እነሱ ቢሄዱም ‴ቢያልፍ ህይወታቸው፣

እስከነ ኩተቱ ይቀራል ጉዳቸው፣

ሲነገር ይኖራል ሥራና ግብራቸው፣

እያነጋገረ ድብቁ አላማቸው።

ከፉ የሠሩና የሠሩ መልካአም፣

ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍም፣

ግብርና ሥራቸው በዚችው ዓለም፣

ሲነበብ ይኖራል ልክ እንደ መቅድም።

ከእግዲህ አቁሙ መዝራት የውሽት ዘር፣

በዝቶብናል እና መከራና ችግር፣

ሲጠፋነው እንጂ መች አየን ሲበቅል፣

ገንጭና እንክርዳዱ ሲደባለቅ ከህል፣

ከግዲህ ይብቃችሁ በጥቅም መደለል፣

የዘመኑ መምህራን ሰባኪያነ ወንጌል፣

ሁለት ሶስት አይደለም አንዲትናት የእሱ ቃል።

ባካችሁ አቁሙ ለሰይጣን ማገልገል፣

ቤተክርስቲያንን ከሁለት መከፈል፣

ስትሉ ሞላናት ዓለምን በወንጌል፣

እኛ ግን አየን በረከቱ ሲጎድል።

EthioLion.Com

አትያዝብን አይተህ ከፉ ሥራችንን፣

የአሁኑን ትውልድ ከእምነት የራቅነውን፣

ለጥንት አባቶች ላለፉት በእምነት፣

ለነሱ ጠብቃት ደጓን ሃይማኖት፣

ደግሞም ሀገራችን ኢትዮጵያን ታደጋት፣

ምንም ለማያውቁት ኃጢአትን ላልሰሩት፣

ለእነሱ ስትል ለሚያድጉት ሕጻናት፣

እኛን ይቅር በለን በሰራነው ኃጢአት።

ታረቀነ ጌታ አብቃን ለንስሐም አብቃን፣

በደላችን ትተህ ምህረት አድርግልን፣

የአንተን መመለኪያ የቃልህን ጽላት፣

ሥጋህና ደምህ የሚፈተትባት፣

አርክሰናልና ያንተን ቅድስት ቤት።

የቤተክርስቲያንን ቃለ አዋዲ እና ቀኖና አፍርሰው ለሰይጣን አገልጋይ ለሆነው ለሐሳዊ መነኩሴ ለአባ ገብረ መድህን ተከታይና አደግዳጊ የሆኑ ካህናት ቤተ እግዚአብሔር ሲቃጠልና ሲመዘበር ሕዝበ ክርስቲያን ሲጨፈጨፍና ከቤት ንብረቱ ሲፈናቀል አይተው እንዳላዩ ሰምተው እንዳልሰሙ በመምሰል ደግሞም በውጭ አገር ያለውን ሕዝበ ክርስቲያን ለሃይማኖቱና ለሀገሩ በአንድ ላይ ሆኖ እንዳይቆም በጥቅምና በሌላ ነገር ደልለውና ከፋፍለው ሰላም የነሱት መነኮሳትና ጳጳሳት ከአለቃቸው ጋር ሁነው ፍርዳቸውን የሚቀበሉበት ጊዜ ደርሶአል። ቤተክርስቲያን ተቃጥላ ፈርሳና ተመዝብራ አትቀርም።

EthioLion.Com